# ኢትዮጵያና እግዚአብሔር

ኢትዮጵያና እግዚአብሔር ስንል ኢትዮጵያና ሃይማኖቷ ማለታችን ነው። ኢትዮጵያ የተባለችው ይህች የእግዚአብሔር የምስጋና ከተማ ከ7ቱ አህጉራት አንዱ በሆነው አፍሪካ የምስራቅ ክፍል ትገኛለች።

ቅዱስ ዳዊት በመዝሙሩ "ኢትዮጵያ ታበጽሀ ዕደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር" መዝ 67 (68) ፥ 31 ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች ብሎ የዘመረበት ምክንያት የእግዚአብሔርና የቅድስት ኢትዮጵያ የግንኙነት ኪዳን የጠበቀ በመሆኑ ነው። ህዝቧ አምላኩን የሚፈራ ሕጉን የሚጠብቅ ጌታ በወንጌሉ እንድተናገረው ዮሐ 20 ፥ 29 "ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዐን ናቸው" ብሎ የኢትዮጵያ ህዝብ በእምነት የተመሰከረለትን ያምላኩን ትእዛዝ የጠበቀ ብፁዕ ህዝብ ነው። ለዚህም ምስክሩ ቅዱሳት መጽሐፍትና የእውነት ታሪክ ናቸው።

እግዚአብሔር አምላካችን የፈጠረውን የሰውን ልጅ ወደ ህይወት ይመለስ ዘንድ በተለያዩ ዘመናት እርሱን የሚያውቅበትን ለእርሱም የሚገዛበትን መንገድ ሰጥቶታል። እነዚህም ሕገልቡና ፣ ሕገኦሪት፣ ሕገወንጌል ናቸው። የሰው ልጅ ፍጥረት ሁሉ አምላኩን ለማወቅ እነዚህ ሕግጋት ይገልፁለታል ከእነዚህ የወጣ የለም።የሚገርመው ነገር እነዚህን አሟልታ በዓለም ላይ ያለች ሀገር ኢትዮጵያ ብቻ ናት።ነገሩ እንዲህ ነው።

## ኢትዮጵያ በሕገልቡና

ሕገልቡና (God's Moral Law) ሕገኦሪት በሙሴ አማካኝነት እግዚአብሔር ለህዝቡ እስከተሰጠበት ጊዜ ድረስ የሰው ልጅ ይጠቀምበት የነበረ ዛሬም የሚጠቀምበት ያልተፃፈ ሕግ ወይም የአእምሮ ፀባይ ነው።

ይህ የአእምሮ ፀባይ ለሰው ልጆች በእግዚአብሔር አምላክ የተሰጠው ታላቅ ፀጋ ስለሆነ ክፋንና ደጉን ፣ ጽድቅና ኩነኔውን ይለይበት ዘንድ የሚያስችለው የሕሊና ሕግ ነው።

ይህን የልቡና ሕግ በእኛ ውስጥ የቀረፀው ገና ሲፈጥረን እንደሆነ ማስተዋል ይገባናል። ዘፍ 2፥7 "እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ"
እንግዲህ ይህች ሕያው የሆነች ነፍሳችን ናት የፈጠራትን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ስለምትረዳ እኛም በእውነተኛ መንገድ እንድንሄድ የምትጠራን ይህም ሕገ ልቡና ነው;; በአጠቃለይ እግዚአብሔር በልባችን የቀረጸው ሕግ ነው።ሐዋርያው ለዚህ ነበር እንዲህ ያስተማረው ሮሜ 2፥14 "ሕግ የሌለባቸው አሕዛብ ከባሕርያቸው የሕግን ትዕዛዝ ሲያደርጉ እነዚያ ግን ባይኖራቸው እንኳ ለራሳቸው ሕግ ናቸውና እነርሱም ሕሊናቸው ሲመሰክርላቸው አሳባቸውም እርስ በእርሳቸው ሲካሰስ ወይም ሲያመካኝ በልባቸው የተፃፈውን የሕግ ሥራ ያሳያሉ።

እንገዲህ ይህንን ያህል ስለሕገ ልቡና ካየን የኢትዮጵያ ሕዝብ በዚህ ሕግ መሠረት እንደተጠቀመበትና አምላኩን እንዳመለከበት ብዙ ግልፅ ማስረጃዎች አሉ ስለዚህ ኢትዮጵያ እግዚአብሔርን የምታውቀው በኦሪት ጊዜ ብቻ ሳይሆን ከዚያ በፊት ነበር ማለት ነው።

ለምሳሌ 1- ሕገ ኦሪት የተሰጠው በሙሴ ነው - ሙሴ ሕግን ከመቀበሉ በፊት እግዚአብሔርን አማኝ ነው - የፈርዖንን ቤት ሹመት የናቀው በእምነት ነው።
(ዕብ 11፥23-28)
ይህ የእግዚአብሔር አገልጋይ ሙሴ ያገባት ሚስቱ ኢትዮጵያዊ እንደሆነች መጽሀፍ ቅዱስ - በኦሪት ዘኁልቁ 12፥1 ይገልፃል።ይህች የሙሴ ሚስት ሲፓራ እግዚአብሔርን ከሚያምን ቤተሰብ የተወለደች ነበረች። ይልቁንም አባቷ የእግዚአብሔር ካህን ነበር - ዘጸ 2፥16-22 እንግዲህ ይህ የሚገልፅልን ኢትዮጵያ ከሕገ ኦሪት በፊት በሕገ ልቡና የእግዚአብሔር ገር መሆኗን ነው።

2.ንግሥተ ሳባ ወይም ንግሥተ አዜብ ተብላ የምትጠራው ኢትዮጵያዊት ንግሥት ብንመለከት እግዚአብሔርን ማመን የጀመረችው ኢየሩሳሌም ሄዳ ከመጣች በኋላ ሳይሆን ከመሄዷ በፊት አስቀድሞ በሕገ ልቡና ፈጣሪዋን የምታውቅ መሆኗን የእግዚአብሔር ቃል ይመሰክርልናል።ኢትዮጵያ በሕገ ልቡና ሀገረ እግዚአብሔር ስለሆነች ንግስቲቷም ወደ ኢየሩሳሌም ወደ ንጉሥ ሰሎሞን
የሄደችበት ምክኒያት በተመሳሳይ እምነት ያለች እሥራኤል በሰሎሞን ምክንያት ያገኘችውን በረከት ለመመልከትና እግዚአብሔርን ለማመስገን ነበር።
መ.ነ.ቀ 10፥9 "አንተን የወደደ በእስራኤልም ዙፋን ያስቀመጠህ አምላክህ እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን" ይህን ማለቷ ንግሥት ኢትዮጵያ እግዚአብሔር ታውቀውና ታመልከው ስለነበር ነው። ለዚህም ነው ጌታችን መድሐኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለእምነት ምሳሌ አድርጎ በወንጌል ያስተማረን እንዲህ ብሎ ......"ማቴ 12፥42 ሉቃ 11፥31

ይህች የኢትዮጵያ ንግሥት በአክሱም መንበሯ እያለች እስከ የመን ድረስ ትገዛ ነበር። ንግስተ ሳባም ከኢየሩሳሌም በተመለሰች ጊዜ ከንጉሥ ሰሎሞን ጸንሳ ምንይልክ (ምኒሊክን) እንደወለደችና በእሱም አማካኝነት የብሉይ ኪዳን እምነትና ሥርዓት ወደ ኢትዮጵያ እንደገባ የአገሪቷ ታሪክ ይመሰክራል።

## ኢትዮጵያ በሕገ ኦሪት

ቀዳማዊ ምኒልክ አባቱን ለመጠየቅ ወደ ኢየሩሳሌም ተጉዞ ሲመለስ ከእርሱ ጋር የተመረጡ 318 ሌዋውያን የብሉይ መምህራን እንዲሁም ደግሞ በፈቃደ እግዚአብሔር የቃልኪዳኑን ታቦት ንጉሥ ሰሎሞንን አሲዞ እንደላከው የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ ይመሰክራል። በዚያን ጊዜ ነው እስከ ሰሎሞን ድረስ የተጻፉ የብሉይ መፃሕፍት ወደ ኢትዮጵያ የገቡት።እንግዲህ ከዚያን ጀምሮ ኢትዮጵያ የኦሪትን እምነትና ሥርዓትን መፈጸም የጀመረችው።

በዚህም ምክንያት ነበር እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ከእስራኤል ያስበለጣት። አሞጽ 9፥7 "የእስራኤል ልጆች ሆይ እናንተ ለእኔ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን?ይላል እግዚአብሔር።"ይህ ምን ይገልጽልናል - አዎን ዛሬ እስራኤል ታቦቱ የላትም። የዚህ ምሥጢር ባለቤት ግን ቅድስት አገር ኢትዮጵያ ናት። በአጠቃላይ አገራችን ኢትዮጵያ ከአንድ ሺህ ዓመታት በላይ የብሉይን እምነትና ሥርዓት ጠብቃ አስጠብቃ እግዚአብሔርን በማምለክ የጸናች አገር ናት - ቅድመ ክርስትና ይህ የብሉይ መስዋዕት የተሰዋባት የነበረች አገር እንደነበረች በሁሉም የአገሪቷ ክፍል ያለ የታሪክ ማስረጃ የባሕልም ምስክርነት አለ። ለምሳሌ - በጣና ሐይቅ አካባቢ የብሉይ መስዋዕት ይቀርብባቸው የነበሩ የንዋየ ቅድሳት ምስክሮች አሉ። ኢትዮጵያ በዚህን ዘመን ለአምላኳ መስዋዕተ ቁርባን ታቀርብ ነበር።ነቢዩ ሶፎንያስ እንዲህ ሲል ትንቢት ተናገረ "ከኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ የሚማልዱልኝ የተበተኑት ሴቶች ልጆቼ ቁርባኔን ያመጡልኛል" ሶፎ - 3፥9

እንዲህ ባለ ሁኔታ ኢትዮጵያ ለአንድ አምላክ እየሰገደች እረሱን ብቻ እያመለከች ሀገረ እግዚአብሔር ሆና አምላክ ከሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ፣ ተሰዶ፣ ተጠምቆ፣ በመስቀል ተሰቅሎ ደሙን አፍስሶ፣ ስጋውን ቆርሶ ዓለምን ሁሉ ያድናል እያለች የተቆጠረው ሱባዔ የተነገርው ትንቢት ይፈጸማል አምስት ሺህ አምስት መቶ የሐጢያት ፣ የጨለማ ዘመን ያበቃል እያለች በእምነት ፀንታ ስትኖር እውነትም ጌታችን እኛን ለማዳን ሰው ሆነ - ክርስትና ተዋህዶ በዚህ ተጀመረች- ኢትዮጵያም የመጀመሪያዋ ክርስቲያን አገር ለመሆን በቃች።

## ኢትዮጵያ በክርስትና

ቅድስት አገር ኢትዮጵያ በሕገ ልቡና በሕገ ኦሪት ስለማመኗ የነገረን መነሻው መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ስለ ክረስትናውም መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል የሐዋሪያት ሥራ 8፥26 " የጌታም መልአክ ፊሊጶስን ተነስተህ በደቡብ በኩል ከኢየሩሳሌም ወደ ጋዛ ወደሚያወርደው ምድረ በዳ ወደ ሆነ መንገድ ሂድ አለው። ተነስቶም ሄደ። እነሆም ህንደኬ የተባለች የኢትዮጵያ ንግሥት አዛዥና ጃንደረባ የነበረ

በገንዘቧም ሁሉ የሰለጠነ አንድ የኢትዮጵያ ሰው ሊሰግድ ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ ነበር።ሲመለስም በሰረገላ ተቀምጦ የነቢዩን የኢሳያስን መጽሐፍ ያነብ ነበር፡... ፊሊጶስም አፉን ከፈተ ከዚህም መጽሐፍ ጀምሮ ስለ ኢየሱስ ወንጌል ሰበከለት ... ሁለቱም ወደ ውኃ ወረዱ አጠመቀውም፡"

እንግዲህ ልብ በሉ -

1ኛ ጃንደረባው አማኝ ነበር፡

2ኛ ወደ ኢየሩሳሌም የሄደው ሊሰግድ ነበር

3ኛ የኢሳያስን ትንቢት ያነብ ነበር

እነዚህ ከላይ ያየናቸው ኢትዮጵያ በብሉይ ኪዳን እምነት የነበረች አገር መሆኗን ሲገልጽ። ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ስንመለከት 1ኛ ፊሊጶስ ስለ ኢየሱስ ወንጌል ሰበከለት

2ኛ ጃንደረባው ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አመነ

3ኛ ተጠመቀ

እነዚህ ደግሞ የክርስትና እምነት የሚገልጹ ናቸውና ኢትዮጵያ በ34 ዓ/ም ጌታ ከሞት ተነስቶ ካረገ በኋላ ክርስትናን እንዳመነች የሚያሳይ የእግዚአብሔር ቃል ነው። የነቢዩ ዳዊት ትንቢት በዚህ ሲፈፀም እንመለከታለን እንዲህ ያለው "ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች።" መዝ 67(68)፥31 ከዚያን ሰዓት ጀምሮ ክርስትና ውስጥ ውስጧን እየተስፋፋች የወልደ እግዚአብሔር ሰው ይሰበክባት ጀመር። ይልቁንም ደግሞ በ330 ዓ/ም ክርስትና የመላው የኢትዮጵያ እምነት በመሆን ብሔራዊ ሆነ። በዚህም ጊዜ በእግዚአብሔር ፈቃድ አባ ፍሬ ምናጦስን እግዚአብሔር በምክንያት ወደ ኢትዮጵያ የመጣው።የግሪክ ዝርያ ያለው አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን የተባለው የመጀመሪያ ጳጳስ ሲሆን የብሉይ ሊቀ ካህናት የነበረው ኢትዮጵያዊ አንበረም ደግሞ የመጀመሪያው ኤጲስ ቆጶስ ነበር። በግብፅ ከፓትሪያርኩ ከአቡነ አትናቴዎስ እጅ አባ ሰላማ ተብሎ እንደ ተሾመ ስለ ኢትዮጵያም የክርስትና እምነት በ4ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ የነበረው የቤተክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ ሩፊኑስ እንዲህ የሚለው ተጽፏል።

በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አብርሃና አጽብሃ የተባሉ ወንድማማቾች አክሱም ነግሰው ሳለ ከአጎቱ ከፈላስፋው ከመሮፔዎስ ጋር ህንድን ለመጎበኘት ሲጓዙ መርከባቸው ስለሰመጠች ከወንድሙ ከሲድራኮስ ጋር ከሞት ተርፎ ምጽዋ አጠገብ የተገኘው የጢሮስ ተወላጅ ግሪካዊው ፍሬምናጦስ ከሕፃንነቱ ጀምሮ ወንጌልን እየተማረ ያደገ ስለነበር ከኦሪቱ ሊቀ ካህናት ከአንበረም ጋር ተመካክሮ የሚያስተምር የሚያጠምቅና የሚያቆርብ ጳጳስ ከእስክንድሪያ ለማምጣት ተላከ። ወደ እስክንድሪያ የተላከው በኢትዮጵያዊነቱ እንጂ በግሪክነቱ አልነበረም። የእስክንድሪያ ፓትሪያርክ አትናቴዎስም የኢትዮጵያን ቋንቋና ልማድ ስለምታውቅ አንተው ጳጳስና ሐዋርያ ነህ ብሎ ሰላማ በሚል ስም ማዕረገ ጵጵስና ሰጥቶ በ330 ዓ/ም ወደ ኢትዮጵያ ሰደደው ይላል።

ይህ የሆነው ከላይ እንደተመለከትነው አብርሃና አጽብሃ በቀድሞ ስማቸው ኤዛናና ሳይዛና በነገሱ ዘመን አንበረም በኤጲስ ቆጶስነት ስሙ ቅዱስ ሊቀ ካህናት በነበረበት ዘመን ነው። አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃንም አባቶች 318 ሊቃውንት የወሰኑትን እምነትና ሥርዓት እያስተማረ የአርዮስንና የመሰሎቹን ምንፍቅና እያወገዘ በመላው ኢትዮጵያ ከኢትዮጵያ መምህራን ጋር በመሆን ወንጌልን ሰበከ። በዚህ ዘመን የተደረጉ፦

1ኛ መጽሐፍ ከግሪክ ወደ ግዕዝ ተተረጎመ

2ኛ በርካታ ቤተክርቲያናት ታነጹ ከዚህም ውስጥ አንዷ ባለ 13 መቅደስ በአክሱም የታነጸች ጽዮን ማርያም ናት።

ከላይ በተመለከትነው ሁኔታ በህንደኬ ጃንደረባ፣ በፊሊጶስ፣ እንዲሁም በወንጌላዊ ማቴዎስ የተሰበከላት ወንጌል እየተስፋፋች ኢትዮጵያ የክርስቲያን ቅድስት አገር ሆነች። እንዲሁም እውነተኛ የኦርቶዶክስ ተዋህዶን የክርስትና ትምህርት የሚየስተምሩ አባቶች አውሮፓ ከፍተኛ ስቃይና መከራ ሲደርስባቸው ወደ ቅድስት አገር ኢትዮጵያ ይሰደዱ ነበር። ጌታስ ከእናቱ ጋር ተሰደባት የለ? ለምሳሌ ከ451 በኋላ በርካታ መነኮሳትና ምዕመናን ወደ ኢትዮጵያ ገብተዋል - ወደ ኢትዮጵያ ከገቡት መካከል እነዚህ ቅዱሳን አባቶች በርካታ ክርስቲያናዊ በረከት ለኢትዮጵያ የሰጡ ናቸው።

1.አባ አሌፍ

2.አባ ጽሕማ
3.አባ አረጋዊ (ዘሚካኤል)
4.አባ አፍጼ
5.አባ ገሪማ (ይስሐቅ)
6.አባ ጰንጠሌዎስ
7.አባ ሊቃኖስ
8.አባ ይምዓታ
9.አባ ጉባ

እነዚህ አባቶች ወደ ኢትዮጵያ የመጡበት ምክኒያት የሮማ ነጉሥ መርቅያንና ንግሥቲቱ ብርክሊያ የአንድ ባሕርይ እምነትን ማለት ኦርቶዶክስን ለማጥፋት ቅዱስ ዲዮስቆሮስን ጋንግራ በተባለ ደሴት አስረው - በጊዜው እነሱን እንደ አምላክ የሚያሳድዷቸውን መናፍቃን ኢየሱስን ሁለት ባሕርይ የሚሉትን በመደገፍ መከራ በክርስቲያን ላይ ስላበዙ ለዚህ ነበር እነዚህ ቅዱሳን አባቶች በእምነት ወደሚመስሏቸው ወደ ኢትዮጵያን የመጡት - በሰሜኑም ክፍል በተለይ በትግራይ ገዳማትን መስርተው እግዚአብሔርን እያመለኩ ኖረዋል። ይህ የሆነው በ5ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ነው።

ክርስትናን በኢትዮጵያ ስናይ ብዙ አስደናቂ ነገሮችን እንመለከታለን። ከዚህም ውስጥ አንዱ የመላዕክት ዝማሬ ለዚህች ቤተክርስቲያን መሰጠቱ ነው - ይህም የሆነው በኢትዮጵያዊው ሊቅ በቅዱስ ያሬድ ነው። ዛሬ ያለው የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ዜማ መሠረት ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን ለያሬድ ይህን ሁሉ የገለጸለት እርሱ ነው።

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን እየተስፋፋች እስከ የመንና እስከ ማዳጋስካር ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና እንደተሰበከች የቤተክርስቲያናችን ታሪክ ይነግርናል። በ6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያው ንጉሥ ካሌብ አይሁድ የየመንን ክርስቲያኖች ሲያሰጨንቁ ዘምተው ደቡብ አረቢያን ነፃ አውጥው እንዲሁም የዐፄ ካሌብ እንደራሴ አብርሃም በየመን ብዙ ቤተክርስቲያን አሳንጿል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ይህንን ሁሉ በምታደርግበት ጊዜ ፈተና ሳይኖርባት አይደለም - ክርስትና ያለ ፈተና አልተመሰረተችም በተለይ ከ7ኛው እስከ 9ኛው መቶ ግብፅ በእስላሞች እጅ ወድቃ ኢየሩሳሌም እንዲሁ በነበሩበት ዘመን የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ከውጪ ያላት ግንኙነት በአብዛኛው ተቋርጦ ነበር።

በ10ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ደግሞ ኢትዮጵያዊቷ አይሁድ ዮዲት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ለማጠፋት ከፍተኛ ዘመቻ ለ40 ዓመታት አድርጋለች። ዘመቻዋም ኢትዮጵያን የአይሁድ አገር ለማድረግ ነበር። ካህናት ታረዱ፣ ዲያቆናትና ምዕመናንም ታረዱ፣ ቅዱሳት መጽሐፍት ተቃጠሉ፣ የመጀመሪያው ቤተክርስቲያን በአብርሃና በአጽብሃ የተሰራው ከሁለት የክርስትና ታሪካዊ ሐውልቶች ጋር ወደሙ።ይህ ሁሉ ፈተና በእምነታችን ተከፈተ። በዚህን ጊዜ ካህናትና ምዕመናን የሚችሉትን ያህል ታቦታትና ቅዱሳት ዕቃዎችን እንዲሁም መጽሐፍትን ይዘው ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ይንከራተቱ ነበር። ዮዲት (ጉዲት) አንዱ አላማዋ ጽላተ ሙሴን ለማግኘት ነበር። በዚህን ጊዜ ግን ካህናት ጽላቱን ይዘው አርሲ ክፍለ ሀገር ዝዋይ ደሴት ተሰደው ነበር። በእግዚአብሔር ክርስቲያኖች ጠንክረው ዮዲትን ድል አድርገው እንደገና ቤተክርስቲያንን በመሰራት፣ ወንጌልን በመሰበክ ጸኑ። ዛሬም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን መልኩን በለወጠ መልኩ እነዚህ ፈታኞች በየጊዜያቱ ይከፍቱባታል - ካህናትም ምዕመናንም እንንቃ።

ነቢዩ ዳዊት የኢትዮጵያ እጆች ወደ እግዚአብሔር ተዘርግተዋል እንዳለ ይህንን እጅ ለማጠፍ ማንም አልቻለ። በ12ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያዊው ቅዱስ ላሊበላ ዛሬ ዓለም የሚደነቅባቸውንና አስራ አንድና ከዚያ በላይ የሆኑትን አብያተ ቤተክርስቲያናት ሕንፃ በመላእክት እርዳታ አንጿል - ይህንንም ለመሥራት 20 ዓመት ያህል አስፈልጎታል። እነዚህም

1. ቤተ መድሃኔዓለም
2. ቤተ ማርያም

3. ቤተ ደናግል
4. ቤተ መስቀል
5. ቤተ ሚካኤል
6. ቤተ ጎለጎታ
7. ቤተ አማኑኤል
8. ቤተ ገብርኤል
9. ቤተ አባ ሊባኖስ
10. ቤተ መርቆርዮስ
11. ቤተ ጊዮርጊስ

ሲሆኑ አብያተ ክርስቲያናት በደብረ ሮሐ (ላሊበላ) አካባቢ የተሰሩ ሲሆኑ ቅዱስ ላሊበላ ከላስታ ውጪ ሌሎችንም አብያተ ክርስቲያናት አንጿል። ከላይ የገለጽነው ቤተ ሊባኖስን ባለቤቱ እቴጌ መስቀል ክብራ እንዳሳነጸች ታሪክ አለ።

በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ደግሞ በርካታ ቅዱሳን ከእግዚአብሔር ለዚህች አገር ተሰጥተው ነበር።በዚህ ጊዜ ነበር ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ አዲስ ሐዋርያ ሆነው በመላው ኢትዮጵያ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል የዘሩት።

በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በዐፄ ዳዊት ዘመነ መንግሥት ከኢየሩሳሌም የጌታ ቀኝ እጅ ያረፈበት ግማደ መስቀሉ ልዩ ልዩንዋየ ቅድሳት ወደ ኢትዮጵያ ገቡ። ይህ ግማደ መስቀል ዛሬ በወሎ ክፍለ ሃገር በአምባሰል ተራራ በደብረ ከርቤ ገዳም ግሸን በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ባሰሩት የእግዚአብሔር አብ ቤተክርስቲያን ውስጥ ተቀምጧል።

በዚህ ዘመን በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ አማካኝነት በርካታ አብያተ ክርስቲያናት ታንጸዋል፣ መጽሐፍት ተተርጉመዋል በዚህ ዘመን የአርዮስን ፣ የንስጥሮስን፣ የመቅዶንዮስን ዓይነት የኑፋቄ ትምህርት ይዘው የተነሱ አባ እስጢፋኖስ የተባሉ መነኩሴና ተከታዮቹ በቤተክርስቲያን ሊቃውንት ተወግዘዋል። ንጉሱም የሞት ቅጣት ፈረደውባቸዋል። ቅዱስ ጴጥሮስ በሐናንያና በሲጳራ ሊቀ ነቢያት ሙሴ በጸተንና በአቤያን እንዳደረጉት (ሐዋ 5፥1-11 ዘፍ 16፥25-35)

በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ደግሞ ቤተክርስቲያናችን ታላቅ ጦርነት ተከፍቶባት ነበር። ይህም በቱርክ የእስልምና መንግሥት አነሳሽነት በምሥራቅ ኢትዮጵያ በኩል የግራኝ መሐመድ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን እምነትና ሥርዓት የማጥፋት ዘመቻ ነበር። ጦርነቱ ለ15 ዓመታት በቤተክርስቲያን ላይ አነጣጥሮ ቢቆይም በእግዚአብሔር እርዳታ ኢትዮጵያውያን ድል አድርገዋል። በነዚህ 15 ዓመታት ውስጥ ግን ቤተክርስቲያናት ተቃጠሉ፣ የቤተክርስቲያን መጽሐፍት ተቃጠሉ ካህናት ፣ ዲያቆናት ምዕመናን ታረዱ - ይህም ጌታችን በወንጌል እንደተናገረው ነው። በዚህ የጦረነት ሰዓት ፖርቱጋል ጥቂት ወታደሮችን ለእርዳታ ልካ እንደነበር ታሪክ ይነግረናል። የፖርቱጋል ካቶሊኮች ይህንን ተጠቅመው እምነታቸውን ለማስፋፋት ይሞክሩ የነበረውም አንዱ አሳዛኝ ሁኔታ ነበር። በጎንደር ዘመነ መንግስትም ዐፄ ሱስንዮስን ካቶሊኮች አታለው ካቶሊክ የኢትዮጵያ ሃይማኖት እንዲሆን በጣሩበት ጊዜ ከፍተኛ እልቂት በምድራችን ተፈጽሟል።ንጉሱም በእግዚአብሔር መዓት ተመትተው በነበሩ ጊዜ የእግዚአብሔር ቁጣ መሆኑን ተረድተው "ሃይማኖት ይመለስ ፋሲል ይንገሥ" ብለው ንስሀ ገብተው ሞተዋል።

ጌታችን መድሐኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ክርስትናን የመሠረተልን ቤተመንግስት ተወልዶ ሳይሆን በበረት ተኝቶ - ተሰዶ፣ በገዛ ወገኖቹ ተፈርዶበት በወንበዴዎች መካከል ተሰቅሎ ነው። ለዚህ ነው በእውነተኛ መሠረት ላይ የታነጸች ቤተክርስቲያናችን ይህ ፈተና የሚመጣባት በማቴ 16፥18 "በዚህች ዓለት ላይ ቤተክርስቲያኔን እሰራለሁ የገሃነም ደጆች አይችሏትም" ስለዚህም ኢትዮጵያና ክርስትና ዛሬ ያሉበት ደረጃ ድረስ ተዋህደው እንዲህ እስከ ምጽአት ይጓዛሉ።

## ክርስትና

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደሙ የመሠረታት ሃይማኖት ክርስትና ተብላ ተጠራለች። ክርስትና ስንል ክርስቶስን መስሎ መኖር በቃሉ መኖር ማለት ነው።ይህንን ቃሉን የክርስቶስን ወንጌል እየሰበኩ ህዝቡን ወደህይወት ዘወር እንዲል ያደረጉ ደቀመዛሙርት ተብለው ይጠሩ የነበሩ የጌታ ሐዋርያትና አርድእት በአንጾኪያ ክርስቲያን ተብለው ተጠሩ። ሐዋ 11፥19-26

ደቀመዛሙርት ወይም ክርስቲያን ስንል ደቀመዛሙርት ለመጀመርያ ጊዜ በአንጾኪያ ክርስቲያን ይባሉ እንጂ አስቀድሞ ጌታ በማቴ 16፥18 "ወዲበ ዛቲ ኮኩሕ አሐንጻ ለቤተ ክርስቲያንየ" በዚህች ዓለት ላይ ቤተክርስቲያኔን እሰራሉ ብሎ ገልጾታል።

ስለዚህ አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም ተወልዶ በመስቀል ተሰቅሎ ደሙን አፍስሶ ቤዛ ሆኖኛል የሚል ሕጉንና ሥርአቱን ጠብቆ የሚኖር ክርስቲያን ተብሎ ተጠራ።

## ኦርቶዶክስ

ብዙዎች ይህንን ስም በተለይ በእምነት የመጀመርያነትን ለመግለጽ ይጠቀሙበታል። ኦርቶዶክስ የሚለው ቃሉ የግሪክ ሲሆን "ኦርቶ" (ኦርቶስ) ማለት ቀጥ ያለ ማለት ሲሆን "ዶክስ" ማለት ደግሞ እምነት ማለት ነው። ስለዚህ ኦርቶዶክስ ማለት ቀጥ ያለ እምነት ማለትን ይሆናል። ይህ ስም በክርስትና ላይ ተጨምሮ የተነገረው ከሀዲያን መናፍቃን የተበረዘና የነቀዘን እምነት እንዲሁም ከወንጌል ውጪ የሆነ የፍልስፍናን ትምህርት ወደ ቤተ ክርስቲያን ለማስገባት በሚጥሩበት ጊዜ ቅዱሳን አባቶች 318ቱ ሊቃውነት አርዮስንና መሰሎቹን አውግዘው እኛ እሱ ጌታችን የመሠረተልንን ሐዋርያት ያስተማሩንን ቀጥ ያለች እምነት ይዘን እንሄዳለን ብለው ሥርዓት ስለደነገጉ እምነታችንም ኦርቶዶክስ ተብላ ትጠራ ጀመር። "የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ የኑሮአቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሉአቸው። ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንና ዛሬ እስከ ለዛላለም ያው ነው። ልዩ ልዩዓይነት በሆነ በእንግዳ ትምህርት አትወሰዱ" ዕብ 13፥7

## ተዋህዶ

ተዋህዶ የሚለው ቃል ደግሞ ቀጥታ የሚያበስረን የአምላካችን የእግዚአብሔርን ሰው የመሆን ምሥጢር ነው። ይህም ገና ያኔ በኦሪት ዘፍጥረት 3፥22 "እግዚአብሔር አምላክም አለ፦ እነሆ አዳም መልካምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ" የሚለው አምላካዊ ቃል የተፈጸመበት የሰው ልጅ የመዳን ዜና ነው።

ተዋህዶ ስንል ማን ከማን ተዋህደ? በዮሐንስ ወንጌል 1፥14 ላይ "ውእቱ ቃል ሥጋ ኮነ" ያ ቃል ሥጋ ሆነ ይባላል ሙሉ ወንጌሉን ስናነብ ግልጽ ይሆንልናል <u>"ያ ቃል"</u> የተባለው አግዚአብሔር ነው፤ <u>"ሥጋ"</u> የተባለ ደግሞ ሰው ነው። ስለዚህ አምላካችን አግዚአብሔር እኛን ለማዳን ሲል ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ። ከቅድስት ድንግል ተወለደ ስንል የሰውን ባህርይ ባህርይው አደረገ። ሥጋም የአምላክን ባህርይ ባህርይው አደረገ። ምን ማለት ነው? ቃል (አግዚአብሔር) ፦ አይዳበስም፣ አይጨበጥም፣ አይዳሰስም፣ አይበላም፣ አይጠጣም፣ አያንቀላፋም፣ አይሞትም ወዘተ... እነዚህ ሁሉ የሚስሙት ለሰው (ለሥጋ) ነው። አምላካችን ከድንግል በተወለደ ጊዜ ግን በተዋህዶ የሰውን ባህርይ የራሱ አደረገ። በአጭሩ የሠራዊት ጌታ አግዚአብሔር ካለአባት ከእመቤታችን ተወልዶ ሥጋን ተዋህዶ በ30 ዘመኑ ተጠምቆ በቀራንዮ ተሰቅሎ በጎልጎታ ተቀብሮ ሞትን ድል አድርጎ ተነስቶ በተዋሃደው ሥጋ ዳግም ለፍርድ ይመጣል በመንግሥተ ሰማያት ለዛላለም ይኖራል ብሎ ማመን የጠራ የተዋህዶ እምነታችን ነው።

"ባሑ አንተ ጸባብ አንቀጸ" ማቴ 7፥13 በጠባቢቱ ግቡ ወደጥፋት የሚወስደው ደጇ ሰፊ መንገዱም ትልቅ ነውና ወደእርሱም የሚገቡ ብዙዎች ናቸው።

እኛም ወገኖች ሆይ፦ አምላካችን በደሙ የመሠረተልንን የነጻች እስከ መጨረሻ አጽንተን ብንይዝና ለሥዓርቷም እየተገዛን ብንኖር የመንግስቱ ወራሾች የሰሙ ቀዳሾች አድርጎ በክብር ያኖረናል"

“የመጀመሪያ አምነታችንን እስከመጨረሻው አጽንተን እንጠብቅ የክርስቶስ ተካፋዮች ሆነናልና” ዕብ 3፥14

“እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ፦ በመንገድ ላይ ቁሙ ተመልከቱም መልካሚቱ መንገድ ወዴት እንደሆነች እወቁ። በእርሷም ላይ ሂዱ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛለችሁ።እነርሱ ግን አንሄድባትም አሉ። “ኤር 6፥16
ጌታችን በመሠረታት፣ ነቢያት በተነበዩላት፣ ሐዋርያት ባስተማሩላት፣ መላእክት በሚቀድሱባት በዚህች እምነት መኖር ቅድስና ነው ነቢዩ እንደተናገረ ብዙዎች አላወቋትም። እኛ ግን እንወቃት ለዚህም የእግዚአብሔር ፈቃዱ የድንግል ምልጃ ከሁላችን ጋር ይሁን አሜን!